# አቋ ሰለባ

የኢጣሊያ ፋሺስት መንግሥት ኢትዮጵያ ላይ ወረራ ባደረገ ጊዜ ከጠላት ጋር ሆነን እናት አገራችንን ኢትዮጵያን እንወጋም ካሉት የኤርትራ ተወላጆች መሀል አንዱ አቋ ሰለባ ናቸው ። በኋላ ቀኛዝማች የተባሉት አቋ ሰለባ በኤርትራ በነበረው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ውስጥ ነበሩ ። አቋ ሰለባ በኢጣሊያ መንግሥት ዘንድ የታመኑና የተከበሩ ሰው ነበሩ ። በኢጣሊያኖች ዘንድ ክብርና ማዕረግ ይኑራቸው እንጂ ያገራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ዘወትር ይከነክናቸው ነበር ። ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ምክር እየሰሙም ይቆጫቸው ነበር ።

አቋ ሰለባ ለኢጣሊያ ታማኝነታቸውን እያረጋገጡ ውስጥ ውስጡን ግን በኢጣሊያ ላይ አድማ ያካሂዱ ጀመር ። አቋ ሰለባ በኢትዮጵያ ላይ ጠላት የሚዶልተውን ዱለታ አጥብቀው የሚቃወሙ 29 ጓደኞች አበጁ ። እነዚህ 29 የኤርትራ ክፍለ አገር ተወላጆችና የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት አባሎች በድብቅ የኢትዮጵያን ያገር ፍቅር ማኅበር አቋቋሙ ። መስከረም 1 ቀን 1928 ዓም የእንቁጣጣሽ ዕለት አቋ ሰለባ በጦር ሠራዊት ውስጥ የጥበቃ ሥራ ወይም የፓትሮልነት ሥራ ተረኛ ሆኑ ። ሌሊቱን በጥበቃ ላይ እንዳሉ የበላያቸው ኢጣሊያዊው ኦፊሰር የመጨረሻውን ጉብኝት እስቲያደርግ ጠበቁ ። የበላይ አለቃቸው ኢጣሊያዊው መኰንን የጥበቃው ሥራ በትክክል መካሄዱንና ሌሊቱም ፀጥ ያለ መሆኑን ካወቀ በኋላ በመልካም ተግባራቸው እነ አቋ ሰለባን አመስግኖና አበረታቶ ወደ መኝታው ሄደ ።

ከዚህ የመጨረሻ ፍተሻ በኋላ ነው አቋ ሰለባና 29 ጓደኞቻቸው የማኅበራቸውን ሥራ የጀመሩት ። 12ኛ ዓመት ቁጥር 2 ኢትዮጵያን አብዘርቨር ስለዚያች ሌሊት ተግባር ሲገልጽ እነ አቋ ሰለባ 13,500 ጠመንጃ ፤ 5 መድፍ ፤ 30 አልፓይን የሚባለውን መድፍ 12 ረጃጅም መድፍ ይዘው ኢጣሊያኖችን ራሳቸውን ባስደነቀ ሁኔታ ለሊቱን ያን መሣሪያ ሁሉ ይዘው ጠፉ ።

በ30 ሰዎች የተመሠረተው የኢትዮጵያ ፍቅር ማኅበር የኤርትራ ተወላጆች አባላት ያን ሁሉ መሣሪያ ይዘው መቀሌ ደረሱ ። በመቀሌ ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ዘንድ ቀርበው ለኢትዮጵያ ለመዋጋት መነሳታቸውንና ኢጣሊያን መክዳታቸውን ነገሩ ። ኢትዮጵያን ከድቶ ለኢጣሊያ አሽከርነት የገባው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ እነአቋ ሰለባን ይዞ ለኢጣሊያኖች ለማስረከብ አስከበባቸው ። እነአቋ ሰለባም በሰው ብዛት የማይወዳደሩትን የደጃች ኃይለሥላሴ ጉግሳን ጦር ለመዋጋት ተዘጋጁ ። በነገሩ መሀል የአክሱሙ አስተዳዳሪ ንቡረዕድ ተሰፋዬ ገብተው ሰለባ ወልደ ሥላሴና ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ እንዲታረቁ አደረጉ ። እርቁ ፤ ሰለባ ወልደ ሥላሴ የያዙትን መሣሪያ በሙሉ ለደጃች ኃይለ ሥላሴ እንዲያስረክቡና ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ደግሞ ከትግራይ በሰላም እንዲወጡ እንዲፈቅድላቸው የሚል ነበር ።

ሰለባ ወልደ ሥላሴ በዚህ እርቅ አልስማማ ብለው ከደጃች ኃይለ ሥላሴ ጋር ለመዋጋት ተዘጋጁ ። የአክሱም ቀሳውስትና መነኩሳት ፣ ንቡረእዱ ጭምር እነ አቋ ሰለባ ገብረ ሥላሴን ተጭነው ስለያዟቸው በእርቁ ተስማሙ ። ከሃዲው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴም እነቀኛዝማች ሰለባ ወልደ ሥላሴ ከኢጣሊያ ዘርፈው ያመጡትን መሣሪያ በሙሉ አስቀርቶ እነኛ ጀግኖች አንዳንድ የታጠቁትን ሽጉጥ ብቻ ይዘው ወደ መሀል ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ተፈቀደ ።

እነ ሰለባ ወደ አምባላጌ ሄዱ ። በአምባላጌም ከደጃች መኩንን እንዳልካቸው ጋር ተገናኙ ። ምግብና ጥይት ተቀብለው ጉዞአቸውን ወደ አዲስ አበባ ቀጠሉ ። የነሰለባ ወደ አዲስ አበባ መጓዝ በከሃዲው በደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ዘንድ እንደ ተሰማ ራያ አዘቦ ውስጥ እንዲፈጁ አድፋጭ ጦር ቀድሞ ጠበቃቸው ። ቆቦን አልፎ ቀውቂ ከሚባል ቦታ ላይ ሲደርሱ ጥቅምት 21 ቀን ያ የታዘዘ ጦር ገጠማቸው ። ከአቋ ሰለባ ሶስት ሰዎች ሞቱ ። አራት ሰዎች ቆሰሉ ። አቋ ሰለባ ክፉኛ ቢቆስሉም እስከ መጨረሻው ጥይት ድረስ ከነኛ ወመኔዎች ጋር ተታኩሰው ጥይታቸው ሲያልቅ ሸሹ ። ከብዙ ድካም በኋላም ደሴ ገቡ ።

ደሴ እንደደረሱ አቋ ሰለባ ወደ አዲስ አበባ ሄደው እንዲታከሙ አስፋው አሊ በሚነዱት አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተላኩ ። አዲስ አበባ ሆስፒታል እንደተኙ የቀኛዝማችነት ማዕርግ ተሰጣቸው ። ሁለት ከፍተኛ ኒሻኖችንም ተሸለሙ ።

የማይጨው ጦርነት በተጀመረበት ጊዜ ቀኛዝማች ሰለባ ገና ማገገማቸው ስለ ነበር የኢትዮጵያ ጦር ወደ ማይጨው ሲዘምት ቀኛዝማች ሰለባ ለጊዜው አዲስ አበባ ከተማን ጠብቁ የተባሉትን ትእዛዝ ቢቀበሉም የኢትዮጵያ ጦር ወደማይጨው ከዘመተ በኋላ ጀግናው ሰለባ የወኔ ለቅሶ ጀመሩ ። ከአለቃቸው ከደጃች ይገዙ ዘንድም ገብተው "ከኤርትራ ተነስቼ ኢጣሊያን ከድቼ እዚህ የመጣሁት ልዋጋ እንጂ ልቀመጥ አይደለም ። ይልቀቁኝ ። በፈቃድዎ ባይለቁኝ በፈቃዴ የማደርገ ውን ላደርግ ነኝ" አሏቸው ። ደጃች ይገዙም የአዲስ አበባን ሹማምንት ሰብስበው ጉዳዩን አዋዩ ። የሰለባን ሁኔታ ያዩና የሚያውቁ ሹማምንት የንጉሡን ትእዛዝ ፈር ተው ሰለባን ላለመልቀቅ ቢያስቡም ሰለባ ግን ቢከለከሉ ጠፍተው መሄዳቸው ስለ ታወቀ በፈለጉበት አቅጣጫ እንዲዘምቱ ተፈቀደላቸው ።

እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ቀኛዝማች ሰለባ የደጃች ይገዙን ፈቃድ እንዳገኙ ያራዳን ዘበኛ ሰብስበው ጃንሜዳ ላይ ያሰለጥኑ ጀመር ። ሥልጠናው ካለቀ በኋላ በጥር ወር 1928 ዓም ልጅ ኃይለ መስቀልን ፤ በጅሮንድ ተክለ ሥላሴን ፤ ቀኛዝማች አሰፋ ባህታን ከነጭፍሮቻቸው ይዘው ከደጃዝማች በየነ መርዕድ ጦር ጋር ተደባ ለቁ ። ወዲያው ቀኛዝማች ሰለባና ቀኛዝማች አሰፋ ባህታ ከጦሩ ተለይተው ለበሽ ዲስ ከተባለው ቦታ የደረሰውን የኢጣሊያን ጦር እንዲወጉ ታዘዙ ። ከታዘዙበትም ቦታ ደርሰው የኢጣሊያን ጦር ድል አድርገው ብዙ ጠመንጃዎች ፤ ምግብ ፤ ልብስ ፤ ገንዘብና በጣም ብዙ ጥይት ማረኩ ። ይህን ሁሉ ምርኮ ይዘው የተረፈውንና የሚሸ ሸውን ጦር ሲያባርሩ 15 የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ያንን ቀበሌ በሙሉ በቦምብ እንዲደበድቡ ታዘው ደረሱባቸው ። እነ ቀኛዝማች ሰለባ ግን ምንም ሳይጐዱ ምርኮአ ቸውን ይዘው ከዋናው የወገን ጦር ጋር ተደባለቁ ።

በማይጨው ጦርነት ድል መሆናችንን ከራዲዮ ሠራተኛው ከአቶ ቴዎድሮስ መንገሻ ሰሙ ። ወደባሌ ሲሄዱ እነበጅሮንድ ተክለሥላሴን አጡ ። ወዴት ሄዱ? ቢሉ በእርሻ እኖራለሁ ብለው ወደ አገር ቤት ሄዱ አሉዋቸው ። ከዚያ በኋላ ቀኛ ዝማች ሰለባ ሲዳሞ ገብተው ሀገረሰላም ላይ ከራስ ደስታ ጦር ጋር ተደባለቁ ። ተፈሪ ኬላ እና አርቤ ጐና ላይ በተደረጉት ጦርነቶች ተካፋይ ሆነው የኢትዮጵያ ጦር ድል ሆነ ። ከዚያም አርበኞቹ ወደ ባሌ ለመሻገር ሲወስኑ ቀኛዝማች ሰለባ አልሄድም ብለው 150 ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ሲዳሞ መሀል ሲመለሱ የኢጣ ሊያ ጦር ገጠማቸውና 15 ቀናት ያህል ተዋጉ ። በኋላም እንደገና ከብረ መንግሥት አካባቢ አርሜራ ከተባለ ቦታ ላይ ከሚያባርራቸው የኢጣሊያ ጦር ጋር ተጋጠሙ ። ከዚያም ግንቦት 24 ቀን 1930 ዓም ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ሲሉ ታላቁ የኢትዮ ጵያ ጀግና በዚያች ጦር ሜዳ ላይ ወደቁ ።

———O———

# መላኩ በያን

መላኩ በያን በብዙዎች ዘንድ ያልታወቀ ፤ ስሙን በሚያውቁት ዘንድም ቢሆን ምን ታሪክ እንዳለው ያልተገለጸለት ለኢትዮጵያ ታላላቅ ሥራ እየሠሩ ከተረሱ ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው ። እኔም ብሆን የመላኩ በያንን ታሪክ በሙሉ እጽፈዋለሁ ለማለት ሳይሆን በመጠኑ ለመግለጽ እሞክራለሁ ።

መላኩ በ1892 ሚያዝያ 21 ቀን ወሎ ክፍለ ሀገር ተወለደ ። አባቱ ግራዝማች በያን ፤ እናቱ ወ/ሮ ደሲታ ይባላሉ ። መላኩ በተወለደ በስድስት ወሩ እናትና አባቱ ወደ ሐረር ሲሄዱ ይዘውት ሄዱ ። በሐረር ከተማ በራስ መኩንን ግቢ የቄስ ትምህርት ሲማር አደገ ።

በተወለደ በ21 ዓመቱ በ1913 ዓም ወደ ውጭ አገር ለሕክምና ትምህርት ሄደ። ዘ ማርች ኦፍ ብላክ ሜን የሚባለው ጋዜጣ መላኩ በያንን አነጋግሮ ታሪኩን ጽፎ ነበር ። "እኔ ለትምህርት የመጣሁት ፍላጐቴን ለንጉሡ ገልጬ ነው ። የምፈልገው የሕክምና ትምህርት ነው ። የሕክምና ትምህርት ተምሬ ከጨረስኩ አገሬ ተመልሼ አንድ የሕክምና ድርጅት አቋቁሜ ያገሬን ሕዝብ ለመርዳት ነው ምኞቴ ብዙ ነገሬ ነው የመጣሁት..." ብሏል ።

መላኩ ለሕክምና ትምህርት ወደ ሕንድ አገር ተላከ ። ብቻውን አልነበረም ። ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት አብረው ነበሩ ። መላኩ በሕንድ አገር ያለው ትምህርት ስላልተስማማው ወደ አሜሪካ ለመሄድ አሰበ ። በተለይ አብራው ለትምህርት የሄደችው ሴቷ ልጅ በመሞቷ መላኩ የሕንድ ኑሮው አላስደሰተውም ። ሁለት ወንድ ጓደኞቹን ይዞ በ1914 ዓም በሚያዝያ ወር በመርከብ ተሳፍሮ ከሕንድ ወደ አሜሪካ ተጓዘ ። አሜሪካ እንደደረሰም ማሪየታ ኮሌጅ ገባ ። 1918 ዓም መላኩ የከፍተኛ ትምህርት ዲግሪውን ሲያገኝ አፍሮ አሜሪካን የሚባለው ጋዜጣ እ.ኤ.አ. መስከረም 14 ቀን 1925 ዓም ባወጣው እትሙ "...በአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያዊ ዲግሪ ተሰጠ ።..." በማለት ጽፎለታል ።

መላኩ በያን በ1920 ዓም ኮሎምቦስ ውስጥ ኦሃዮ እስቴት ዩኒቨርሲቲ ገባ ። ከዚያም አንድ ዓመት ከተማረ በኋላ ወደ ሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ዞሮ የሕክምና ትምህርቱን ቀጠለ ።

ዘማርች ኦፍ ብላክ ሜን የተባለው ጋዜጣ መላኩን ባነጋገረው ጊዜ መላኩ እንዲህ አለ "...ሃዋርድ ዩኒቨርሲቲን የመረጥኩበት ምክንያት ከአገሬ ሰዎች ጋር ለመገናኘት የሚያመቸኝ በመሆኑ ነው ። ዋነኛው ነገር ደግሞ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ልጅ ጋር ልንጋባ ተጫጭተን ስለነበር ያን የጋብቻ ውል ለመሰረዝና ከጥቁርዋ አሜሪካዊት (ዶሬቲ ሀድሊይ) ጋር ለመጋባት የቢታሁበት መሆኑ ነው." ብሏል ።

በሰኔ ወር 1928 ዓም ከሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ መላኩ በያን በዶክተርነት ተመረቀ ። ያ ዘመን ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት የከፈተችበት ጊዜ ስለነበረ ዶክተር መላኩ በያን አገሩን ለመርዳት በተመረቀ ወር ሳይሞላው ሐምሌ 3 ቀን ሚስቱን ወይዘሮ ዶሬቲን እና ልጁን ይዞ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞውን ጀመረ ። በጉዞ ሰንብቶ ሐምሌ 25 ቀን አዲስ አበባ ገባ ። አዲስ አበባ እንደደረሰ ለጊዜው በአሜሪካ ሚሽን ሆስፒታል ሥራ ቢጀምርም ጦርነቱ እየተፋፋመ በመሄዱ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ውስጥ ተመዝግቦ አጋዶን ዘመተ ።

የኢጣሊያ ፋሽስት አዲስ አበባን ሲይዝ መላኩ በያን ቤተሰቡን ይዞ በ1928 ዓም ወደ እንግሊዝ አገር ሄደ ። ከዚያም ወደ አሜሪካ ሄዶ ስለ ኢትዮጵያ በግፍ መወረር እየሰበከ ርዳታ ይለምን ጀመረ ። በሮክላንድ ፓላስ ሁለት ሺህ ሰዎች በተሰበ መስከረም 2 ቀን 1929 ዓም ባደረገው ንግግር "...አገራችንን የምንለቅ ሕዝቦች አይደለንም ። ጠላቶቻችን የያዙብንን መሬት ለቀው እስኪወጡ ድረስም ወታደሮቻችን ተኩስ አያቆሙም ። ጥቁር ያሸንፋል..." በማለት የተሰበሰበውን ሕዝብ እንዴት እንደቀሰቀሰ ዘማርች ኦፍ ብላክ ሜን የተባለው ጋዜጣ ጽፎለታል ።

ፕሮፌሰር ሀሮልድ ኢስሐቅ ስለመላኩ በያን ሲመሰክሩ ኒውምርልድ ኦፍ ኔግሮ አሜሪካንስ በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ ብለዋል ። "...በስደት ያሉት የኢትዮጵያ መኳንንትና ንጉሡ ባላቸው ንቀት ምክንያት ከጥቁሮች ጋር እንነጋገርም እያሉ የመላኩን ስብከት ባያደናቅፉ ኖሮ ኢትዮጵያን ለመርዳት የተነሣው ጥቁር አሜሪካዊ ቀእምር በሥራ ነበር..."

መላኩ በግብፅ ፣ በጅቡቲ ፣ በኬንያ ፣ በሱዳንና በሌላም ቦታ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ለመርዳት "ምኒሊክ ክበብ" ስለሚባለው ድርጅት ፣ ቮይስ ኦፍ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ድምፅ) ስለተባለው ጋዜጣው ፣ በያንዳንዱ ሰው ቤት እየዞረ ስለሚያደርገው ልመና ፣ ዩናይትድ ኤይድ ፎር ኢትዮጵያ በማለት ስላቋቋመው ድርጅት ፣ ገንዘብ ለማግኘት ሲል የኢትዮጵያን ምስል እያሳተመ ስለሸጣቸው ቴምብሮች ሁሉ ዘርዝሬ ማውራት አልችልም ።

መላኩ በያን እያሳተመ ስለሚሸጠው ቴምብር አምስተርዳም ኒውስ የተባለው ጋዜጣ ወኪል ጠይቆት መላኩ ሲመልስ ፣ "....ነፃነት ያላቸው ስለባርነት አያስቡም ፣ ሆዳቸው የሞላም ስለረሃብ አይነጋገሩም..." ብሎ መልስ መስጠቱን እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 2/1937 ዓም በወጣው እትሙ ገልጾታል ።

ዶክተር መላኩ በያን ቀላል ሰው አልነበረም ። በላቲን አሜሪካ እና በዌስት ኢንዲስ የማኅበሩን 22 ቅርንጫፎች አቋቁሞ ስለ ኢትዮጵያ የለፋ ወጣት ነበር ። በያንዳንዱ የማኅበሩ ቅርንጫፍ ያሉት አባሎች በሺ የሚቆጠሩ ነበሩ ።

በነሐሴ ወር 1931 ዓም ታመመ ። ነሐሴ ሲያልቅ በሽታው ተሻለውና ያንኑ የትግል ሥራውን ጀመረ ። እንደገና በመጋቢት ወር 1932 ዓም ቤት ለቤት እየዞረ እርዳታ ሲለምን በኒሞኒያ በሽታ ተለከፈ ። በጠና ስለታመመ ሮክላንድ እስቴት ሆስፒታል ገባ ። ሚያዝያ 26 ቀን 1932 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ።

በአሜሪካና በሌላም አገር ያሉ ታላላቅ ጋዜጦች የመላኩን መሞት በታላቅ ኀዘን ጻፉለት ። ያቋቋመው ቮይስ ኦፍ ኢትዮጵያ ጋዜጣም እ.ኤ.አ. ሜይ 11/1940 በወጣው ቁጥሩ "ወጣቱና ታላቁ መሪ ሞተ..." በሚል ርዕስ ጻፈለት ።

አገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ በ40 ዓመት ዕድሜው ተቀጨ ።

———O———

# አድዋ

ወደፊት የሚገሰግሰው የኢጣሊያ ጦር መስከረም 25 ቀን 1928 ዓም አዲግራትን ያዘ ። አዲግራት ከተያዘ በኋላ ከአዲግራት እንትጮ ፣ ከእንትጮ አድዋ የሚያደርስ የመኪና መንገድ መሥራት ተጀመረ ። የመንገዱ ሥራ የሚከናወነው ሌት ከቀን ነበር ። ወታደሩና መንገድ ሠሪው ክፍል በመደዳ በሰልፍ ቆሞ "ከሮም እስከ አዲስ አበባ" የሚለውን መዝሙር እየዘመረ እጅ በጅ ድንጋይ ይቀባበላል ። ከኢጣሊያ ወታደር ፊት ለፊት አምሳ ማይል ያህል ራቅ ብለው 20 000 ወታደሮች ይዘው የተቀመጡትን ራስ ሥዩምን የሚያስባቸውም ሆነ የሚጨነቅላቸው ኢጣሊያዊ የለም ። በስተሰሜን 40 000 ወታደር ይዘው የተሰለፉትን ራስ ካሣንም የሚያስታውስ ኢጣሊያዊ ጠፋ ። ኢጣሊያኖች ሁለቱንም የጦር መሪዎች ንቀው የመንገድ ሥራቸውን ቀጠሉ ።

የምድር ጦሩ መንገዱን በሚሠራበት ጊዜ የኢጣሊያ አየር ኃይል አድዋ ከተማ ድረስ በመብረር ሕዝቡን ያስፈራራ ነበር ። ጋዜጠኛው ቼስኮ ቶማሴሊ "... ዴስፔራታ የሚባሉት አይሮፕላኖቻችን ከአግረኞቻችን ጦር ቀድመው እየሄዱ የጠላትን ሠፈር ይመታሉ ። በ0820 ሰዓት አድዋ ከተማ ላይ ሲያንዣብቡ ፣ ከአድዋው ግቢ ፀረ አይሮፕላን ተተኮሰ ። ከየቤቱ ሁሉ መትረየስ ወደ አይሮፕላኖቻችን ይተኰሳል ። ነገር ግን አይሮፕላኖቻችን በአድዋ ከተማ ላይ ሶስት ጊዜ ሲያንዣብቡ ሊያግዳቸው የቻለ ኃይል የለም ። ከአይሮፕላኖቻችን የሚጣሉት ቦምቦችና የሚተኰሱት መትረየሶቻችን በመሬት ላይ ከከተማዋ ይተኮስ የነበረውን ተኩስ እያበረደው ከተማዋን ጭስ ብቻ አደረጋት ..." በማለት ጽፍዋል ።

እንደ ቶማሴሊ አፃፃፍ ከተማዋ ቃጠሎ ይነሳባት እንጂ በሰው ላይ የደረሰ ጉዳት የለም ። አምስት ሺ ያህል የሚሆነው የአድዋ ከተማ ሕዝብ ከተማዋን ለቅቆ ሸሽቶ ስለነበር የኢጣሊያ ቦምብና መትረየስ የገደለው አንዲት ሴት ፤ አንድ ሕፃንና ጥቂት ከብቶችን ነበር ። ከቦምቡ ውርወራ በኋላ የታተሙ የስብከት ወረቀቶች ከአይሮፕላን ተበተኑ ። የተበተኑትም ወረቀቶች "...በሰላም አርፋችሁ ሥራችሁን ሥሩ። ለዚህ ፍትህ ፤ ነፃነትና ሰላም ለሚያስገኝላችሁ ለኢጣሊያ ድል አድራጊነት ድሉ ቶሎ እንዲያልቅ ፀልዩ ። የኢጣሊያ ወታደር የመጣው ለእናንተ ሰላም ሊያስገኝ ነው... የመጣነው እነዚህን ወንጀለኞች ጌቶቻችሁን ለመቅጣት ነው..." የሚል ቃል የያዘ ሲሆን ሕዝቡ በአሰተኛ ወሬ እንዳይሸበርና ችግር እንዳይፈጥርም ያስጠነቅቃል ።

የኢጣሊያ ጦር አድዋን በቀላሉ አልያዘም ። በደጃዝማች ገብሬ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር የኢጣሊያን ጦር አግዶ ተዋግቶ ነበር ። ይህን የኢትዮጵያን ጦር የፈታው ከአይሮፕላን የሚጣለው ቦምብና አይሮፕላኖቹ የሚተኩሱት መትረየስ ነው ። ይህም ቢሆን የሙሶሊኒ ጦር መረብን ካቋረጠ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢጣሊያዊ ወታደር በኢትዮጵያውያን የተገደለው በአድዋ ጀግኖች ነው ። በመደበኛው ጦር የብርጌድ አዛዥ የነበረው ሌተና ሞርጋንቲኒ ከአድዋ ጀግኖች በተተኰሰ ጥይት ተገደለ ። ሞርጋንቲኒ እንደተገደለ ወታደሮቹ በመሪያቸው ሞት ተደናግጠው ቦታቸውን ለቀው ሲሸሹ በነሱ ቦታ 3ኛው ባታሊዮን ተተካ ።

የኢጣሊያ ሰላይ ቡድን ወደ አድዋ ሄዶ ሰልሎ ሲመለስ የአድዋ ከተማ ባዶ መሆኑንና ራስ ስዩምም ያለመኖራቸውን ተናገረ ። ከዚህ በኋላ ከዳር ተቀምጦ የነበ

ረው የ84ኛው ሬጂሜንት 2ኛ ብርጌድ መስከረም 26 ቀን 1928 ዓም ከጧቱ አራት ሰዓት ላይ አድዋ ከተማ ገባ ። ይህ ብርጌድ አድዋ ከተማ ሲገባ ሙዚቀኞች በሰልፍ ሆነው ሙዚቃ እያሰሙ የኢጣሊያን ባንዲራ አስይዞ ገባ ። የብርጌዱ አዛዥ ቪላ ሳንታ ፈረስ ላይ ሆኖ በመኰንኖች ታጅቦ ከወታደሩ ኋላ እየተጓዘ ወደ ራስ ስዩም ግቢ ሄደ ።

ቪላ ሳንታ በአስተርጓሚ ንግግር አደረገ ። "....ከዚህ በኋላ ቦምብ የለም ። የሽፍት ዘመዶቻችሁም ይመለሱ ። ኢጣሊያ መብታችሁን በሙሉ ትጠብቃለች..." አለ ። ቪላ ሳንታ ንግግሩን ሳይጨርስ አምስት ኢትዮጵያውያን ተኩስ ከፈቱበት ። ከእነዚህም ከአምስቱ አንደኛው እዚያው ሲገደል አራቱ አመለጡ ።

የሶስተኛው አየር ኃይል ብርጌድ አዛዥ ጄኔራል ራንዛ የአድዋን መያዝ በቴሌግራም ለደቦኖ አሳወቀ ። ጄኔራል ደቦኖ በ4 ሰዓት ተኩል የአድዋን መያዝ እንደሰማ በ5 ተኩል ገደማ "ኩሩዎቹ ኢጣሊያኖች በኩራት አድዋ ገቡ" የሚል ቴሌግራም ወደሮም አሳለፈ ። ሙሶሊኒ የአድዋን መያዝ ሲሰማ ተደሰተ ። "ለእንተና ለወታደሩ ሁሉ የከበረ ምስጋና በኔና በሕዝቡ ስም አቀርባለሁ" የሚል መልስም ለዶቦኖ ላኩለት ።

አድዋ የተያዘው በቀላሉ አይደለም ብያለሁ ። የኢትዮጵያ ወታደር ባለው ውልክስክስ ጠመንጃና ጥይት 30 የኢጣሊያ ወታደሮችን ገድሎ 70 አቁስሏል ። 33 የኢጣሊያ ወታደሮች ጠፍተዋል ። ይህ ቁጥር ራሳቸው ኢጣሊያኖቹ ያመኑት ነው ። አድዋ ከተያዘ ከጥቂት ቀናት በኋላ ማለት ጥቅምት 3 ቀን አክሱም ተያዘ ። ከጥቂት ቀናት በኋላም የአክሱም ሐውልት "የድል አድራጊው የፋሽስት መንግሥት መታሰቢያ" ተብሎ ተወሰደ ።


ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውጋት ጦር ሲያግዙ ከጦሩ ጋር አንድ ከእብነ በረድ የተሠራ ሐውልትም ከሮማ መጥቶ ነበር ። ሐውልቱ በጋቪናና ዲቪዢን ሲጓዝ ከርሞ አድዋ እንደተያዘ በዱቼ ሙሶሊኒ ትእዛዝ በምኒሊክ ጊዜ አድዋ ላይ ለተገደሉ ኢጣሊያኖች መታሰቢያነት ተተከለ ። ይህንንም የመታሰቢያ ሐውልት ጄኔራል ደቦኖ መርቆ ከፈተው ።

ኢጣሊያ አድዋና አክሱምን ከያዘ በኋላ አልደላውም ። ለስብከት ብሎ የሚነዛውን ገንዘብ ሕዝቡ በደስታ አልቀበል አለ ። በተለይ ከኤርትራ ተቀጥረው የዘመቱለት ወታደሮቹ ማለት የኤርትራ ተወላጆች በብዛት ከድተው ከነመሣሪያቸው ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ስለተደባለቁ ከባድ ስጋት አደረበት ። ደቦኖም ከዚያን ጊዜ በኋላ የነጭና የጥቁር ወታደሮችን ማለያየቱ ቀርቶ ባንድነት ተደባልቀው እንዲዘምቱ አደረገ ። ይህም ነጮቹ ጥቁሮቹን እንዲጠብቁ ነው ።

———o———




በኢጣሊያ አይሮፕላን ፎቶግራፍ የተነሳው የአድዋ ከተማ



የኢጣሊያ ጦር አክሱምን ለመያዝ ተጓዘ።



የኢጣሊያ ሠራዊት አዲግራትን ለመያዝ ሲገዝ



አዲግራት በቀላሉ አልተያዘችም

# መቀሌ

አድዋና አክሱም ከተያዙ በኋላ የኢጣሊያ ወታደር የነበሩ የኤርትራ ተወላጆች ከኢጣሊያ እየከዱ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ስለገቡ ሙሶሊኒ በጣም ተበሳጨ ። የኤርትራ ተወላጆች መክዳት መጥፎ አደጋ መሆኑን ስለተረዱም ሹምሽር አደረጉ ። በዚህ ሹም ሽርም ኤሌሳንድሮ ሌሶና የቅኝ ግዛት አገሮች ኃላፊ ሆኑ ። ማርሻል ባዶሊዮም የምሥራቅ አፍሪካ ጦር ቺፍ አፍ ስታፍ ሆኖ ተሾመ ። ሌሶና ያን ጊዜ በያዙት ማስታወሻ "...ይህን ሁሉ ነገር ያመጣው ሙሶሊኒ በኤርትራ ሰዎች መክዳት ጉዳይ ደቦኖን ስለጠረጠረው ነው..." ብለዋል ። ሙሶሊኒም ለአሌሳንድሮ ሌሶና ሲያጫውት "...አንተን ባዶሊዮ ያግዝሃል ። ነገሩን አሁን በሚስጢር ያዘው እንጂ ደቦኖ ተሽሮ ባዶሊዮ ተሹሟል..." ብለዋል ።ሌሶናም በኋላ ማለት እ.ኤ.አ. ሰኔ 9 ቀን 1936 ዓም የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ተብለው ተሹመዋል ።

ሙሶሊኒ ከደቦኖ ጋር ጠብ ሲፈልግ "....እስከ ኅዳር ከትግራይ ባሻገር ያለውን አገር ሁሉ ገፍተህ እንድትይዝ" የሚል ቴሌግራም አሳለፉ ። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ "...ኖቨምበር 5 ቀን ከትግራይ ግዛት ወጥተህ ወደፊት ግፋ..." የሚል ትእዛዝ አዘዙ ። የጨነቀው ደቦኖም "...የጌታዬን ትእዛዝ አልቀበልም አልልም ። ወደፊት ለመግፋት ግን ብዙ ችግርና አደጋ ያጋጥማል ። አሁን እንኳ ከስንቅ ሠፈር 90 ኪሎ ሜትር በመራቃችን ችግር አለ..." ሲል መለሰ ። ሙሶሊኒም "...ስለፖለቲካ ጉዳይ መነጋገር አልሻም ። ከዚህ በፊት ኦክቶበር 3 ግፋ ብዬ ያዘዝኩሁ ጥሩ ውጤት አምጥቷል ። አሁንም ኖቨምበር 3 ቀን ከመቀሌ እስከ ተከዜ እንድትይዝ አዝዣሃለሁ" አለ ። እነኚህን ምልልሶች ደቦኖ በመጽሐፉ ጽፎአቸዋል ።

መቀሌን ለመያዝ በሚደረገው ፍልሚያ ተካፋይ ለመሆን ከኢጣሊያ አዳዲስ የመኳንንት ጦር መጥቶ ነበር ። ልዕልት ሜሪ ጆሴ በቀይ መስቀል ነርስነት ፤ የቤርጋሞ ልዑል ፤ የአኦስታ ልዑል ፤ የስፖሊቶ ልዑል በየመኳንንቶቻቸው እየታጀቡ ከጦራቸው ጋር ተደባለቁ ። ደቦኖም በመጽሐፉ "...ወደ መቀሌ ለወረራ ከመጓዛ ችን በፊት የቤርጋሞ ልዑል የጦሩ ምክትል አዛዥነት ተሾሞ የግራሳሶ አዛዥ ሆኖ መጣ ። ....እሱ ብቻ ሳይሆን የፒስቶያው ልዑልም የ23ኛው ማርዞ ዲቪዥን አዛዥ ሆኖ መጣ ።...ከእነኚህም ሌላ የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አባል (ሴኔተር) ሱአርዶ እና ብዙ የሕግ መምሪያው ምክር ቤት አባላት ፥ የፋሺስት ፓርቲ ታላላቅ እውቅ አባ ላት ፤ ምሁራን ሁሉ መጡ ። ማሪኒቲ ብቻ እንደነገ ልንዘምት በዋዜማው ማታ የልብስ ሻንጣውን ብቻ ይዞ ከኔ ዘንድ ደረሰ ..." ሲል ገልጾዋል ።

ዱቼ ሙሶሊኒ ባዘዘው መሠረት የኢጣሊያ ጦር መቀሌን ለመያዝ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 3 ቀን (በኛ ጥቅምት 23 ቀን) ተንቀሳቀሰ ። ጦሩ ሲንቀሳቀስ የተሰጠው ድልድል የማራቪኛ ጦር መሀል ለመሀል ቀድሞ በመጓዝ ምሽግ እንዲያዘጋጅ ሲታ ዘዝ በጄኔራል ሳንቲኒ የሚመራው 1ኛው ዲቪዚዮን ከአዲግራት በስተደቡብ አድ ርጎ መቀሌ እንዲገባ ፤ በጄኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ የሚመራው ጦር ደግሞ በሀውዜን አድርጎ ከሳንቲኒ ጦር ጋር መቀሌ እንዲገናኝ ተደረገ ። ከዚህም ሌላ ከሳንቲኒ ጦር በስተግራ ተወርዋሪ ብርጌድ ከምጽዋ ተነስቶ በደንከል በረሃ አቋርጦ በረሃውን እያ ሰሰ መቀሌ እንዲደርስ ታዘዘ ።

እነኚህ ሶስቱ ጦሮች በያቅጣጫቸው ተጉዘው በዚያኑ ዕለት ማታ ገደማ መቀሌ ለመድረስ 30 ማይል ያህል ቀራቸው ። ከተነሱ ጀምሮ በሰላም ተጓዙ ለማለት ሳይ

ሆን ጠንከር ያለ አይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ግጭት አጋጥሟቸዋል ። የኢጣሊያ አይሮፕላኖችም በመቀሌ ከተማ ላይ እንዣብበውና ሰልለው መቀሌ ከተማ ውስጥ የተዘጋጀ የኢትዮጵያ ጦር መኖሩን አሳወቁ ። ቶማሴሊ ስለቀዳሚው ጦር ሲገልጽ "...ቀዳሚው ጦር ጉንዲ ተራራ ላይ ሲወጣ ከሥራችን መቀሌና የመቀሌ አካባቢ ታየን ። በሜዳው ላይ ሊታጨድ የደረሰ ቢጫ ሰብል በነፋስ ይወዛወዛል ።የማሽላው ሰብል ገና አልደረቀም ። ውብ የሆነው የሚዘናፈለው ነጭ ጤፍና ባቄላው ሁሉ ገና እሸት ነው ። መንገድ የሚመሩና አብሬ ያለኋቸው የጉግሳ (ኃይለሥላሴ ጉግሣ) ሰዎች መቀሌ! መቀሌ! እያሉ ጮሁ ። ኢጣሊያኖችም በሙሉ ተደስተው ወደፊት ይጣደፉ ጀመር ..." ብሏል ።

300 የሚሆኑ ሌሎች ቆራጥ ኢትዮጵያውያን ግን መንገዱን ዘግተው በተን ቀሳቀሰው የኢጣሊያ ጦር ላይ ተኩስ ከፈቱ ። በዚህ ተኩስም ሁለት የኢጣሊያ መኰንኖች ክፉኛ ሲቆስሉ ሌሎችም ተገደሉ ።

እንደ ዱቼ ሙሶሊኒ ትእዛዝ ኖቬምበር 3 ቀን መቀሌን መያዝ ያለበት ጦር በጀግኖች ኢትዮጵያውያን አልበገር ባይነት መንገዱን ስለዘጉበት ኖቬምበር 6 ማለት ጥቅምት 26 ቀን ድረስ የኢጣሊያ ጦር ሲዋጋ ቆየ ። ጥቅምት 27 ቀን ጧት የኢጣሊያ አይሮፕላኖች የመቀሌን ከተማ ሰልለው ከተማው ጦር የሌለበት ባዶ መሆኑን ስላሳወቁ ቀዳሚው ጦር መቀሌ ከተማ አጠገብ ደርሶ ሠፈር አድርጎ አደረ ። በኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የሚመሩ ወታደሮችም የመቀሌን ከተማ ዙሪያ ከበው ሲጠብቁ አደሩ ።

በማግሥቱ ጥቅምት 28 ቀን ጠቅላላው የኢጣሊያ ጦር ባንድ ጊዜ ተነስቶ ሙዚቀኞች ሙዚቃ እያሰሙ መቀሌ ከተማ ገባ ። ሌላው ጦር አደጋ ሳያጋጥመው መቀሌ ይግባ እንጂ በብርጋዲየር ጀኔራል ኦሬስቶ ማሪኦቲ የሚመራው ጦር ግን ከባድ ጦርነት ገጥሞት ከብዙ እልቂት በኋላ ነው መቀሌ ሊገባ የቻለው ።


ኢጣሊያኖች መቀሌን በያዙ በሶስተኛው ቀን ሙሶሊኒ ለዶቦኖ "ሳትዘገይ ወደ አምባላጌ ገስግስ" የሚል ቴሌግራም አሳለፉለት ። ደቦኖም "...ወደ አምባላጌ ለመሄድ ብዙ ችግር አለ ። ለጦርነት ታክቲክም አያመችም ። የሚጠቅመው ዘር ያውን መክበቡ ነው..." የሚል የቴሌግራም መልስ ላከ ። ደቦኖ ይህን መልስ ከላከ ከስድስት ቀናት በኋላ ከዱቼ ሙሶሊኒ አንድ ቴሌግራም ደረሰው ። ቴሌግራሙም "...ያንተ መልእክት ተፈጽሟል ። ባንተም ቦታ ባዶሊዮ ተተክቷል..." የሚል ነበር ።

ማርሻል ባዶሊዮ ኅዳር 17 ቀን አስመራ ገባ ። ሙሶሊኒ ባዶሊዮን የሾሙበት ዋና ምክንያት ባዶሊዮ ሁል ጊዜ በዲስኩርም ሆነ በሚያስተላልፈው ቴሌግራም "ጠላት መጠረግ አለበት" ይል ስለነበር ጠላት የሚሉንን ኢትዮጵያውያንን እንዲጠራርግ ተብሎ ነው ። በእርግጥም እውነት ነው ። እስከሁን ድረስ ማለት በደቦኖ የጦር አመራር ጊዜ ያልተጣለ የመርዝ ጢስ ፣ ሥራ ላይ የዋለው ባዶሊዮ የጦር አመራሩን ከያዘ በኋላ ነው ። ስለዚሁ ጉዳይ ሊኦናርድ ሞስሊ ሲጽፍ "... ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የጦርነቱ ሁኔታ ተለወጠ ። ...ማንኛውም የኢትዮጵያ ነገር ሁሉ በቦምብ እንዲደበደብ ተወሰነ ። ከተማዎች ፤ መንገዶች ፣ ሆስፒታሎች ፤ የቀይ መስቀል ድርጅቶች ሁሉ የየዜጋቸው ባንዲራ በግልጽ እየታየ በቦምብ ተደበደቡ..." ብሏል ።


———O———




ለምር እቅድ የተነሳው የመቀሌ ፎቶግራፍ



ወደ መቀሌ የሚጓዘው የኢጣሊያ ጦር የአጉላን ወንዝ ሲሻገር



መቀሌን ለመያዝ ከባድ ውጊያ ተደርጓል



የኢጣሊያ ወታደር ወደ መቀሌ ሲገዝ



የደጀኑ ወደ መቀሌ ሲጓዝ



የመቀሌ ሕዝብ በርትቶ በመዋጋቱ የኢጣሊያ ወታደር አምባጉር ኮረብታን ያልፈው በእንቶቅቅ ነበር።




አምባ ወርቅ ላይ የተደረገው ውጊያ



ካሚቼ ኒሪ (ባለጥዊር በሥጊዘ) ወደመቀሌ ሲጓዝ



"በፍጥነት ወደ መቀሌ።"




መቀሌ ተወረረች።




የመቀሌ ምሽግ በኢጣሊያ ተያዘ ።




መቀሌ ከተያዘች በኋላ ዙሪያዋን በእሾካማ ሽቦ ታጠረች ።




መቀሌ ዋና የጦር አይሮፕላኖች ማረፊያ ሆነች።




መቀሌ ዋና የስንቅና ትጥቅ ማከፋፈያ ሆነች።



መቀሌ ላይ የተቋቋመው የቁስለኞች ማከሚያ የድንኳን ሆስፒታል።




መቀሌ ላይ የተከማቸ የጅ በምብ ፡ እያንዳንዱ በምብ ሁለት ኪሎግራም ይመዝናል።



የመቀሌ አዲግራት መንገድ በአስቸኳይ ተሠራ ።



በመቀሌ አዲግራት መንገድ ላይ የተሠራ የአስቸኳይ ጊዜ ጊዜያዊ ድልድይ ።



የመቀሌው ጉዞ ።



የመቀሌ አገባብ ።

# ተምቤን

የራስ ሙሉጌታ ፤ የራስ ካሣና የራስ ሥዩም ጦር መደዳውን ሠፍሮ የኢጣሊያን ጦር በሁለት በመከፈል መቀሌን ለማስለቀቅ ተሰለፉ ። ራስ ሙሉጌታ ከሠፈራቸው ከአምባራዶም ተራራ 3ኛውን የኢጣሊያ ክፍለ ጦር እንዲመቱ ተወሰኖ ራስ ካሣና ራስ ስዩም በተንቤን ሜዳ ላይ የሠፈረውን የኢጣሊያን ጦር እያስለቀቁ ፣ ወደ ሐውዜን እንዲገፉ ተወሰነ ። ውሳኔው ይወሰን እንጂ የኢትዮጵያ ጦር የሚገናኝበት ራዲዮ ስለሌለው ያንዱን መግፋት ወይም መጠቃት ሌላው ጦር ሊያውቅ አይችልም ነበር ።

የመገናኛ ራዲዮ ያላቸው ራስ ካሣ ብቻ ነበሩ ። የእሳቸውም ራዲዮ የሚያገለግለው ከንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ለመገናኘት ብቻ ነው ። በኢትዮጵያ ጦር በኩል ያለው ችግር የመገናኛ ራዲዮ ብቻ አልነበረም ። ከቤቱ ጩብጦ የያዛት ጭብጦና የአሹቅ ስንቁ ሳይዋጋ በመጉላላት አልቃበታለች ። ሠራዊቱ ሕይወቱን ለማቆየት ያህል ጥሬ ቆጥሮ ከሚበላበት ደረጃ ደርሷል ።

ይህን የመሳሰለውን በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ የደረሰውን ችግር ባዶሊዮ አሰልሎ አውቆታል ። ስለዚህ ይህን የራዲዮ መገናኛ የሌለውንና ስንቁ ያለቀበትን ሠራዊት ለያይቶ ለማጥቃት ወሰነ ። ጥር 11 ቀን 1928 ዓም ጧት በጄኔራል ባስቲኮ የሚመራው 3ኛው ብርጌድ ከመቀሌ ተነስቶ ነብሪና ነገዳን ይዞ አምባራዶም ወዳለው ወደራስ ሙሉጌታ ጦር ተጠግቶ ፣ ራስ ሙሉጌታ ለራስ ካሣ እንዳያግዙ መንገድ እንዲዘጋ አዝዞ እንቀሳቀሰው ። ይህ ጦር ጥር 11 ቀን ቦታውን ከያዘ በኋላ በማግሥቱ ተምቤን ያለው ጦር ውጊያ እንዲጀምርና እንዲከላከል አዘዘ ። በስተግራ በኩል ደግሞ 2ኛውን ክፍለ ጦር ከሁለት ክፍሎ ባለጥቁር ሸሚዞችን የያዘው ቬንቲ አቶ ዲቬችሮን ወደበለስ እንዲገፋ አዘዘ ።

ከዚህ በኋላ ባዶሊዮ ሠራዊቱን ሰብስቦ የራስ ሙሉጌታ ጦር ስላለበት ስለ አምባራዶም ሲገልጽ "...እስካሁን የተዋጋችሁትን እንደ ትልቅ ውጊያ አትቁጠሩት ። ወደፊትም ትልቅ ጦርነት ይገጥመናል ብላችሁ አታስቡ ። ትልቁ ውጊያችን የአምባራዶው ነው ። በአምባራዶም የተቀመጠው ሽማግሌ የዋዛ አይደለምና በርትታችሁ ተዋጉ ..." ብሎ አዘዘ ።

የባዶሊዮ የጦር ፕላን ተዘጋጅቶና ሠራዊቱም ታዞ ካለቀ በኋላ ራስ ካሣ በራዲዮ ለንጉሡ "...የኢጣሊያን ጦር እንቅስቃሴ እንዲቆርጡ የላከኋቸው ሰዎች በጥሩ ሁኔታ የጠላትን ጦር ከበውታል ..." ብለው አስተላለፉ ። የባዶሊዮ የራዲዮ ሠራተኞች የኢትዮጵያን ራዲዮ ይጠባበቁ ነበርና ይህን የራስ ካሣን መልእክት ጠልፈው ለባዶሊዮ አቀረቡ ። ባዶሊዮም ይህን ሚስጥር ካወቀ በኋላ የነበረውን የጦር ፕላን ለዋወጠ ።

የዋሪዋን በር ይዞ ይጠባበቅ የነበረው በጄኔራል ዱአማንቲ የሚመራው ጦር በአስቸኳይ ወደፊት እንዲገፋና የራስ ስዩምን ጦር እንዲመታ አዘዘ ። ይህም የታዘዘው ጦር ገፍቶ ከራስ ስዩም ሠራዊት ጋር ውጊያ ጀመረ ። የራስ ስዩም ሠራዊትም በአስደናቂ ሁኔታ የኢጣሊያን ጦር ድል አድርጎ ወደኋላ መለሰው ። እያባረረም ብዙ መንገድ ሸኘው ። በዚህም ውጊያ ከኢጣሊያ ሠራዊት 335 ሰዎች ሞቱ ። ጦርነቱንም ሊያቆም የቻለው የጅምበርዋ መጥለቅ ነው ። በዚህ ሁኔታ የባዶሊዮ አዲሱም ሆነ ነባር እቅዱ ከሸፈ ። ያለውን ጦር በሙሉ ወደፊት እንዲገፋ አዘዘ ። ኢትዮጵያውያንም

ወንክረው ሶስት ቀን ሙሉ ተዋጉ ። ውጊያው በተጀመረ በ3ኛው ቀን ኢትዮጵያው
ያን ድል አድርገው ጠቅላላው የተረፈው የኢጣሊያ ጦር በየምሽጉ እየገባ ተከተተ ።

ስለዚያች ጊዜ ሁኔታ አናሊ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና በሚባለው መጽሐፍ
ቮሊዩም 2 ላይ እንደሚነበበው "...አዲስ አበባ ውስጥ በኢትዮጵያ መንግሥት
ወረቀቶች ታትመው ለሕዝብ ተበተኑ ። እነኝህም ብትን ወረቀቶች...ድል አደረግን ።
በጄኔራል ዲያማንቲ የሚመራው ጦር ተበታተነ ። 28ኛው ብርጌድ ጦር ሸሸ ። የኢጣ
ሊያ ታላላቅ ሹሞች የነበሩት ሹም አበራ ፤ ሹም እርባዋስ እና ሹም ካሣ በኛ ወታ
ደሮች ተያዙ... ጥር 12 ቀን ድል አድራጊዎቹ ወታደሮቻችን 29 መድፍ ፤ 175 መት
ረየስ ፤ 2764 ጥይት የተጫነባቸው በቅሎዎችና ሌላም ብዙ የተለያዩ ዕቃዎች ማር
ከው ከጠቅላይ ጦር ሠፈር አስገቡ ። ከዚህም ሌላ ብዙ ምርኮኞችን አስረው እምቁ
ተዋል... የሚሉ ነበሩ ። በዚህ በተገኘው ድል በመደሰት ሌላው ተረሳ..." ይላል ።

ይህ ታላቅ ድል ከተገኘ በኋላ የጦር አዛዥ የነበሩት ራስ ሙሉጌታ
ተሽረው በእሳቸው ምትክ ራስ ካሣ የሰሜን ጦር አዛዥ ሆነው ተሾሙ ። በዚህ
ሹም ሽር የኢትዮጵያ ጦር መከፋፈል ጀመረ ። ትናንት አዛዥ የነበሩት ራስ ሙሉ
ጌታ ዛሬ የራስ ካሣ ታዛዥ መሆናቸው ከፋቸው ። ትናንት የሰሜን ጦር አዛዥ
የነበሩት ራስ ሙሉጌታ ፤ ዛሬ በጦር ጭፍራቸው ታዛዥ ሆነው "...ወደ ሀውዜንና
ወደ አድዋ በሚደረገው ጉዞ ድጋፍ ሰጭ ሆነው እንዲዘምቱ..." ብለው ራስ ካሣ
አዘዙዋቸው ። ጥራላቸው የወደቀው ራስ ሙሉጌታም "እሺ" ብለው ቁጭ አሉ ።
ባዶሊዮም በመጽሐፋ ስለዚህ ሁኔታ ሲገልጽ "...ግራ አጋብቶንና አስቸግሮን የነ
በረው የጠላት ጦር በአዲሱ ሹም ሽር እፎይ የሚያሰኝ ሁኔታ ፈጠረልን..." ብሎ
ታል ።

በራስ ሙሉጌታ የጦር አመራር ጊዜ በዋሪው ምሽግ የነበረው የኢጣሊያ ጦር
በውሃ እጦት ከባድ ችግር ደርሶበት የነበረው አሁን መፈናፈኛ አገኘ ። ስለውሃው
ችግር የጦሩ አዛዥ ጄኔራል ቢካቻንቲ ( Bicaccianti ) " ... ውሃ የለንም ።
የቀረን ጥቂት ሊትር ውሃ ብቻ ነው ። ውሃ የሚጠጣ ማገኛውም ወታደር ውሃ በጥጥ
ላይ አድርጎ ከንፈሩን ያርስ..." ብሎ አወጀ ። የኢጣሊያ ሠራዊት በውሃ ጥም ማለቁን
እውቆ ሳለ አሁን የላላ ከበባ በማግኘቱ ከምሽጉ ወጣ ። ጦሩ ከምሽጉ ሲወጣ በራስ
ካሣ ልጆች በአበራ ካሣና በወንድወሰን ካሣ ፤ በበጅሮንድ ለጥይበሉ ፤ በደጃዝማች
አድማሱ የሚመራው ጦር ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተደባልቆ የጨበጣ ውጊያ ጀመረ ።
በዚህም ውጊያ ብዙ የኢጣሊያ ሠራዊት ወደቀ ።

በዚህ ውጊያ ላይ አባ ሬጂናልዶ ጁሊያኒ ተገደሉ ። አባን ያነሳሁበት ሁለት
ምክንያት አለኝ ። 1ኛው ፤ የኢጣሊያን ጦር እየባረኩ ግፋ ይሉ የነበሩና የሚሸሸውን
እየገዘቱ ይመልሱ የነበሩ ቄስ በመሆናቸው ሲሆን ፣ 2ኛው ፤ የኢትዮጵያውያንን የጎ
ራዴ አመታት እንዴት እንደሆነ ባለውም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ ለማሳወቅ
ብዬ ነው ። እኛው ለእኛው የምንመሰክረው ሳይሆን ጠላት ራሱ የመሰከረውን
መስማቱ የሚያኮራ ነው ።

ዶክተር አልቨርቶ ሉክሲያ የተባሉት ኢጣሊያዊ ሐኪም ጁሊያኒ ፔርክሪስቶ
ኢ. ፔር. ላ. ፓትሪያ በሚባለው መጽሐፋቸው ስለ ፓድሬ ሬጂናልዶ ጁሊያኒ
ሞት ሲገልጡ "...የፓድሬ ሬጂናልዶ ጁሊያኒን ሬሣ ከጦሩ ሜዳ ላይ ጃንወሪ 25 ቀን
(በኛ ጥር 16) ጧት አገኘሁት ። የለበሱት ጥቁር ቀሚሳቸው በተከበረው ደማቸው
ተበክሏል ። የግራ ትከሻቸው አጥንት ለሁለት ተከፍሏል ። ትከሻቸውን እንዲህ አድ
ርጎ ለሁለት የከፈለው መሣሪያ ፣ አበሾቹ ጎራዴ የሚሉት ነው ። በወታደሩ ውስጥ
የአባትነታቸውና የባራኪነታቸው ምልክት እንዲሆን በቀሚሳቸው የደረት ኪስ ላይ
የነበረው መስቀል በጐራዴው ምት ከትከሻቸው ጋር ለሁለት መሀል ለመሀል ተከ
ፍሏል..." ብለዋል ።

የኢጣሊያ ሠራዊት ያለቀው አልቆ የተረፈው ከምሽጉ ከገባ በኋላ የጦር ሠፈሩን እንዳያሰስ እድርጎ ያዋጋ የነበረው ማርሻል ባዶሊዮ የደከመውን ጦር ለማጠናከር ሁለት ባታሊዮን ጦር ባስቸኳይ ላከ ። ባዶሊዮ ስለዚያች ጊዜ ሁኔታ በመጽሐፉ ሲገልጽ "...ዋናው ጥረታችን የመቀሌ መንገድ እንዳይያዝብን ነበር ። የመቀሌው መንገድ ከተያዘ ከባድ ችግር ብቻ ሳይሆን ከባድ እልቂትም ይደርስብናል ። 70 000 ወታደርና 14 000 እንስሳት አሉን ። እነሱም ምግብና መና የሚያገኙት ከመቀሌ ነው ። ለሶስት መቶ መድፎች ጥይት የምናገኘውም ከመቀሌ በመሆኑ ነው..." ብሎታል ።

በተምቤን ምድር አራት ቀን ሙሉ ስለተካሄደው ጦርነት ራፋኤል ቺያስካ ሲጽፍ "... ዳግማዊ አድዋ ሆንዋል ..." ብሏል ። በዚያን ጊዜ ስለነበረው ስለ ባዶሊዮ ጭንቀትም ፓውሎ ሞኔሊ "...በዚያች ጃንወሪ 23 (በኛ ጥር 14) ምሽት ወደ መኝታ አልጋው መሔድ አልቻለም ። ሙሉ የጦር ልብሱን እንደለበሰ ነው ። ኬፒውን አላወለቀም ። ከድንኳኑ ውስጥ ባለው ቴሌፎን አጠገብ ካለው በርጩማ ላይ ተቀምጧል ። ለምንም ነገር ስልኩ ሲጮህ ማዳመጫውን ያነሳና በፀጥታ ያዳምጣል ። ጭልጭል በምትለው መብራት ፊቱ ሲታይ ማስክ ያደረገ ይመስላል ። እንዲችው እንደሆነ ነግቶ ፀሐይዋ ፍንጥቅ ስትል ስልኩ ጮኸ ። በዚያም ስልክ ይጠብቀው የነበረውን ወሬ ሰማ ። ከዚያ በኋላ ተዝናና ። ፈገግታውና ደስታውም በከንፈሩ ንቅናቄ ይታወቅበታል ። ከመቀመጫውም ተነስቶ ወደ ውጭ ወጣና የተለመደውን የጧት ጂምናስቲኩን ይሠራ ጀመር..." ብሏል ።

ባዶሊዮ ይጠብቀው የነበረው ወሬ በጀኔራል ቫካሪስ (Vaccaris) የሚመራው ጦር ዋሪው በር መድረሱን ማወቅ ነበር ። ባዶሊዮ የደከመ ጦሩን በአዲስ ጉልበትና ባዲስ መሣሪያ ካጠናከረ በኋላ ውጊያው እንዲጀመር አዘዘ ። እግረኛው ጦር ከመቅደሙ በፊት የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ስንቅም ሆነ ምትክ የሌለውን የኢትዮጵያን ሠራዊት በቦምብና በመትረየስ ደበደቡት ። እንደ ደቦና ጊዜ ድብደባው በደረቅ ቦምብ ብቻ ሳይሆን የመርዝ ጋዝ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ተረጨ ።

ስለዚያች ጊዜ ሁኔታ ራስ ካሣ ለንደን በነበሩበት ጊዜ በሐምሌ ወር 1928 ዓም የተናገሩት ኡን ቪቶሬ ዴላ ሲቪሊሲሽን የተባለው መጽሐፍ አትሞታል ። እንዲህ አሉ "....ወታደሮቹ መሣሪያቸውን የጣሉት አይሮፕላኖች ቦምብ ከጣሉብን በኋላ ነው ። በተጣለው የመርዝ ጋዝም ወታደሩ ተቃጠለ ። መሣሪያውን እየጣለ የሚያቃጥለውን አይኑን በእጁ እያሸ ተቀመጠ ። አንዳንዱም ከቆመበት በርከክ ይልና በዚያው ወድቆ ይሞታል ። በሰዎቹ ላይ መርዝ ጋዝ እንደ ዝናብ ዘነበባቸው ። የመርዙ ዝናብም የሚያባራ ሳይሆን እየተከታተለ የሚዘንብ ነበር ። ነገሩም የማናውቀው አዲስ መሣሪያ ነበር ። በዚያች ባንዲት ቀን ጥር 15 ቀን ብቻ የሞተውን የሠራዊቴን ብዛት ለማወቅ ያስቸግራል ። ጋዙ ሚዳውንና ጫካውን ሁሉ አቃጠለው ። በትንሹ ሁለት ሺህ ያህል እንስሳት ሞተዋል ። በቅሎዎች ፣ የቀንድ ከብቶችና በጎች ፣ የዱር አራዊቶች ሁሉበስቃይ አልቀዋል ። በማግሥቱም ፣ እንደገና በማግሥቱም ፣ በሶስተኛውም ቀን የኢጣሊያ አይሮፕላኖች በሠራዊቴ ላይ እየተመላለሱ የመርዝ ጋዝ ረጩበት ። ምንም አይነት እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሕይወት ያለው ነገር ባለበት ቦታ ሁሉ በማከታተል የመርዝ ጋዝ ረጩበት..."

የተምቤኑ የመጀመሪያው ጦርነት በእንዲህ ዓይነት የቦምብና የጋዝ መርዝ ፣ የመድፍና የመትረየስ ውርጅብኝ ጥር 16 ቀን ከመገባደዱ ደረሰ ። ኒውዮርክ ሄራልድ ትሪቡን ጋዜጣ እንደፃፈው በዚያ ቦታ በተምቤኑ ግጭት 250,000 ኢትዮጵያውያን በመርዝ ጋዝ ሞተዋል ይላል ። በጣም የበዛ ቁጥር ነው ። ባዶሊዮ ግን በመጽሐፉ "...በአራቱ ቀን ጦርነት 8000 ኢትዮጵያውያን ገደልን። ኢትዮጵያውያን የሚተኩሱት መድፍ ፣ የሚጥሉት ቦምብም ሆነ የመርዝ ጋዝ የላቸውም ነበር" ይልና "... በኛም በኩል ቢሆን 60 የጦር መኰንኖች ፣ 605 ኢጣሊያዊ ወታደሮችና 417 የቅኝ ግዛት ወታደሮችን ኢትዮጵያውያን ገድለውብናል..." ብሏል ።

በውኸግራ፣ በስናኔ የሚዋጋው የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘመኑ እጅግ በጣም ዘመናዊ ከሆነ መሣሪያና ወታደር ጋር ገጥሞ ምን ያህል እንዳስጨነቀ እንገነዘባለን ። የሚገርመው ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር የሚዋጋው ከሞት ያተረፈው ብቻ እንጂ ከኋላ የሚደርስለት ድጋፍ ወይም አዲስ ጦር አልነበረም ። በነጠላው ጫፍ በቋጠራት ስንቁና በቅል በያዛት ውሃ ለኢጣሊያ ጦር አልበገር ብሎ ኢጣሊያን ከተምቤን አላሳልፍ አለ ።

ለሁለተኛው ጊዜ ውጊያ የኢጣሊያ ጦር በአዲስ ኃይልና በአዲስ ጉልበት ተዘጋጀ ። ባዶሊዮም በመጽሐፉ "… ዳግመኛውን ጦርነት ለማዘጋጀት ጊዜ አላባክንኩም ። በቅኝ ግዛት ታሪክ ውስጥ ይህ ጦርነት ተወዳዳሪ የሌለው ነው ። 250 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያለውን የወሰን መስመር በአምስት ዲቪዚዮን ጦር ማስጠበቁ እንኳ ሌላ ከፍተኛ ተግባር ነው ።…" ብሏል ። ባሁኑ ጊዜ ባዶሊዮ ሁለት መቶ ሺ የተጠናከረ ጦር አለው ። ከዚህ ውስጥ ያስፈለገውን ያህል እየከፋፈለ ማሰለፍ ይችላል ። የኢትዮጵያ ወታደር ግን ምትክ ስለሌለው ለዳግመኛው የተምቤን ጦርነት የተሰለፈው ከመጀመሪያው ጦርነት ከሞት የተረፈው ነው ።

ለሁለተኛው የተምቤን ጦርነት ባዶሊዮ 48.000 የመድፍ ጥይትና ሰባት ሚሊዮን የመትረየስ ጥይት መደበ ። 3ኛውን ክፍለ ጦር ወደ ጋሉላ ልኮ የራስ ካሣ ጦር ከራስ ስዩም ጦር ጋር እንዳይገናኝ መንገዱን ዘጋ ። የቅኝ ግዛት ወታደሮችንም ወደ አባሮ ልኮ የራስ ስዩም ሠራዊት ወደፊት እንዳይገፋ አገደው ። በዚህ ጊዜም ራስ ካሣ "…. አሁን ያለንበት ቦታ ለእልቂት የተጠመድንበት ስለሆነ ተምቤንን ለቅቀን እንሂድ…" የሚል የራዲዮ መልዕክት ለንጉሡ አሳለፉ ። ንጉሡም "ወደኋላ አፈግፍጋችሁ የተረፈውን የራስ ሙሉጌታን ጦር ጨምራችሁ አምባላጌ በር ላይ ተጠባበቁ" ብለው አዘዙ ። ባዶሊዮ ባሉት የራዲዮ ሠራተኞች ይህን የራስ ካሣን የራዲዮ ጥያቄና የንጉሡን መልስ ከሰማ በኋላ የጦር እቅዱን አሻሻለው ። 3ኛው ዲቪዚዮን ጦር የገባን ወንዝ ሸለቆውን እንዲይዝ አደረገ ። ለጦርነቱ አመቺ የሆነችው አምባወርቅ ኮረብታ ግን በራስ ስዩም ሰዎች በመያዟ 3ኛው ዲቪዚዮን ወደ አቢአዲ ማለፊያ ተቸገረ ።

አምባ ወርቅ ተራራን ከራስ ስዩም ሰዎች ለማስለቀቅ አልፒን ከተባሉት ተራራ ወጭ ወታደሮች 180 ሰዎች ከባለጥቁር ሸሚዝ ወታደሮች ጋር ሆነው ቦምብና ጩቤ ይዘው የካቲት 19 ቀን በጭለማ ወደ አምባወርቅ ኮረብታ ሄዱ ።—— በማግሥቱ የካቲት 20 ቀን የአምባወርቅ መንገድ ስለተከፈተ የኢጣሊያ ወታደር ሌሊቱን ጭምር ወደፊት መጓዝ ጀመረ ። አንዳንድ ቦታዎችንም ያዘ ።

ከጧቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን በኢትዮጵያውያን ጦር ዘንድ የነጋሪትና የመለከት ድምፅ ተሰማ ። የነጋሪቱ ድምፅ እንደተሰማ ኢጣሊያኖቹ ሳያስቡና ሳይጠረጥሩ የኢትዮጵያ ሠራዊት ደብረ አንሳ ኮረብታን ወርሮ ታላቅ እልቂት አደረሰ ። ስለዚያች ዕለት ሁኔታ ቶማሴሊ እንደፃፈው "…ከጧቱ ጀምሮ እስከ አሥር ሰዓት ድረስ ኢትዮጵያኖቹ የአልፒንና የፋሺታ ኔራን የወደፊት መንገድ ለመዝጋትና ለመጨረስ ከፍተኛ ተጋድሎ አደረጉ ። …እነኚህ የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚተኮስባቸውን መትረየስ ከምንም ሳይቆጥሩ እንደ እብድ እየተሯሯጡ ይገቡበታል ።…" ይላል ።

ኢትዮጵያውያኖች ድል አድርገው ድል የሆነው የኢጣሊያ ሠራዊት መሸሽ እንደጀመረ ደጀን የነበረው በጄኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ የሚመራው ሠራዊት ደርሶ ኢጣሊያውያንን ከእልቂት አዳነ ። ባዶሊዮም "… አደገኛ ጊዜ ነበር ። የሚቀርበውን በመትረየስ፣ የራቀንን በመድፍ እንደበድባለን ። አይሮፕላኖቻችን 195 ቶን የሚመዝኑ ከፍተኛ ፈንጂ ቦምቦችን ኢትዮጵያውያን ላይ ጥለውባቸዋል ።… አበሾቹ በዚያ በእሳት መሀል ጐራዴና ጩቤ እየያዙ እየሮጡ ይመጡብናል ። ወደኛ እየሮጡ የሚመጡትም ብዙ ሬሳዎችን እየዘለሉ ነው ። ሁሉንም ነገር ጉዳይ አይ

ሉትም ።... ፀሺ የሚቆጠር ሬሣ ወድቋል ።..." በማለት ስለዚያች ቀን ጦርነት ጽፏል ።

ባዶሊዮ እንዳለው ብዙ የኢትዮጵያውያን ሬሣ ወድቋል ። ከጦር አዝማቾች መሀልም የደጃዝማች መሸሻ ወልዴና የደጃዝማች በየነ ሬሣ ወድቋል ። መከራው እየበዛ ስለሄደ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደኋላ እንዲመለስ ታዘዘ ። ሠራዊቱም መመለስ እንደጀመረ አይሮፕላኖች እየተከታተሉ ይደበድቡት ጀመር ። ከቦምብ ጣዮች አንደኛው አሌሳንድሮ ፓቮሊኒ ለጋዜጠኞች የሰጠው መግለጫ ማርች 3 ቀን 1936 ዓ.ም. በወጣው ኮሪየሬ ዴላ ሴራ በተባለው ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ነበር ። እንዲህ ይላል "....ኢትዮጵያውያኖች ተበታትኑ ። ሊሄዱ የሚችሉባት መንገድ አንድ ብቻ ነች ። ያቺም መንገድ ጠባብና አስቸጋሪ ናት ። በመንገዳቸው ላይ እንደ ግድግዳ የተገተረ ድንጋይ ሲያጋጥማቸው ትፍግፍግና ትርምስ ይፈጠራል ። እኛም የምንበረው በአንድ ሺ ሜትር ከፍታ ስለነበር ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ይታየናል ። የኢትዮጵያውያኖችን መተረማመስ ስናይ አይሮፕላኖችን እየተምዘገዘገ ቁልቁል ይወርድና ዘሩን በዚያ ትፍግፍግ ሕዝብ ላይ ይዘራል ።......"

አምባ ወርቅ የሰፈረው የራስ ካሣ ጦር በገባ ወንዝ አድርጎ ወደሰቆጣ ለመሻገር ጉዞ ጀመረ ። ከራስ ስዩም ጦር ጋርም ወደ ተከዜ ተጓዘ ። ከራስ ካሣ ጋር የነበረው የጦር አማካሪ ኮናቫሎፍ እንደጻፈው "....ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመሄዳችን አብዛኛው ሠራዊት ከትውልድ አገሩ ከሸዋ የሚገባ መሰለው ።... አብዛኛው ግን በቦምብና በመትረየስ ተደብድቦ ከዚያው ቀረ።..." ብሏል። የራስ ካሣና የራስ ስዩም ሠራዊት ከሁለት ሣምንት የመከራ ጉዞ በኋላ ከንጉሡ ጠቅላይ ሠፈር ከኮረም ደረሱ። በዚህ ጊዜ የዘመተው ሠራዊት ከቤቱ ከወጣ አምስት ወሩ ስለሆነ ተሰላቸ ። ረሃብም ጠናበት ። አንዳንድ መኳንንቶችም እየከዱ ለኢጣሊያ ይገቡ ጀመር ። አንዳንዶችም እየተያዙ ታሰሩ ።

በዚህና በሌላውም ምክንያት የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል ሆኖ የተምቤን ጦርነት የካቲት 22 ቀን አለቀ ። ጦርነቱ አለቀ ቢባልም እንዲና ኮረብታ ፥ እንዳማርያምና ዲቡቅ ያለው ከሞት የተረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት የኢጣሊያን ጦር ገትሮ በመዋጋት እስከ የካቲት 27 ቀን ድረስ ቦታውን አልለቀቀም ። ባዶሊዮም በመጽሐፉ ሲመሰክርላቸው "...ብዛት የሌላቸው የጠላት ወታደሮች በየዋሻው ውስጥ እየተደበቁ ችግር ፈጠሩብን ። ወደ ደቡብ የሚለፈያችንን መንገድ ዘግተው እየተታኮሱ አላሳልፈን አሉ ።... ጥቂር ሰይጣኖች..." ብሏቸዋል ።

ኢጣሊያኖቹ ስለሁለተኛው የተምቤን ጦርነት ባወጡት መግለጫ ስምንት ሺ ኢትዮጵያውያን ገድለን አቁስለናል ብለው ስለራሳቸው ሲናገሩ ደግሞ 34 መኰንኖች ፥ 379 የኢጣሊያ ወታደሮችና 188 የቅኝ ግዛት ወታደሮች እንደተገደሉባቸው ገልፀዋል ።


ተምቤን ውስጥ ከተካሄዱት ጦርነቶች በኋላ ጀኔራል ፋልዴላ ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ ኢስቶሪያ ኢሉስትራታ ላይ እንደጻፉት «....የመርዙን ጋዝ የተጠቀምንበት ከመጀመሪያው የተምቤን ጦርነት ጀምረን ነው ። በእንደርታም ጦርነት ላይ በመርዝ ተጠቅመናል ።...» በማለት መስክረዋል ። ጀኔራል አርሜሊኒ ደግሞ "...ጦርነቱ ቀላል ጦርነት አልነበረም ፤ የኛን ሠራዊት ድል ለማድረግ ያበቃው የተምቤኑና የአሸንጌው ሐይቅ እልቂት ነው ። በማናውቀው አገር ገብተን ወታደር ሳይሆን እንደ አውሬ ከሚመስል ጦረኛ ሕዝብ ጋር መዋጋቱ ቀላል ነገር አልነበረም ፤ የመርዙ ጋዝ ባይኖር ኖሮ ሁለተኛው አድዋ ይደገም ነበር።....» ብለዋል፡

ጠቅላይ የጦሩ አዛዥ ማርሻል ባዶሊዮም «....ከበፊቱ ጀምረን ያውከናል ብለን ያሰብነው የራስ ሙሉጌታ ጦር ነበር ። አሁን ቡተገኘው ድል የአዲስ አበባ


ካለ በኋላ ስለራሱ ወታደሮች ሁኔታ ሲገልጽ
መንገድ ወለል ብሎ ተከፍቷል...» ሰባ ሺ ወታደርም በ280
«...ለዚህ ጦርነት ያሰለፍኩት ሰባ ሺ ወታደር ነበር ፡፡ ይህ የተጠናከረ ነበር ፡፡...
መድፎች ፣ በ170 አይሮፕላኖችና በሺ በሚቆጠር መኪናዎች መንገድ ለማስከፈትና
ወታደሮቻችን የተዋጉት በጥሩ ዋራል ነው ፡፡ የአምባራዶምን ዝግጅት አቅር
ተምቤን ውስጥ ለተካሄደው ጦርነት ለወታደሮቻችን አስፈላጊውን የጣሳ ወተት ፣
በናል ፡፡ ለዚያ ጦርነትም አምስት መቶ ሺ የጣሳ ሥጋ ፣ 150.000 የጣሳ ወተት ፣
150,000 ጠርሙስ የተጣራ ውሃ ፣ 990 ኪሎ ግራም ማርመላታ ፣ 500ሄክቶ ሊትር
ኮኛክና አኒቼ (ነጭ አረቄ) ፣ 700.000ሊሞናድ (ለስላሳ መጠጥ) ለወታደሮቻችን
ዋራል ማዳበሪያ አቅርበናል ፡፡...» ብሏል ፡፡

ለኢጣሊያ ወታደሮች የቀረበው ይህ ከሆነ ለኢትዮጵያዊው ሠራዊትስ በጂ
ኔራል አጉስቲኒ ጦር ውስጥ የነበረው ሳንድሮ ቮልታ ሲገልጽ «...የተዋጋነው ጦር
ነት አይደለም ፡፡ የኢትዮጵያ ወታደር በውሃ እጦት ስለተቸገረ ለኛ አመቺ ሆነልን፡፡
የኢትዮጵያ ወታደር ውሃ ውሃ ውሃ እያለ ወደ ወንዙ በብዛት እየሮጠ ይመጣል፡፡
ከወንዙ ዳር ያሉት ወታደሮቻችን ያለ ምንም ማንጣጠር መትረየሶቻቸውን እየተ
ኩሱ በመቶ የሚቆጠሩትን ባንድ ጊዜ ይፈጁዋቸዋል ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን እልቂትም
ኢትዮጵያውያኖቹ ሳይፈሩ መሣሪያቸውን እየጣሉ ውሃ ለማግኘት ብቻ እየሮጡ
ይመጡብን ነበር፡፡ ...የኢትዮጵያ ወታደር ዝግጅት ስላልነበረው ፈጀነው...» ብሏል፡፡
የኢትዮጵያ ወታደር ከአዝማቹ ይልቅ ሕይወቱን ለማዳንና ለመዋጋትም የረዳው የአ
ገሪቱ የተፈጥሮ አቀማመጥ ነበር ፡፡ ይህንንም ባርቶር ሲመሰክር«..ኢትዮጵያውያ
ዋችን ከመድፍና ከአየር ወረራ የብዙዎቹን ሕይወት መከላከያ ሆኖ ያተረፋቸው ተፈ
ጥሮ የሰጣቸው ምሽግና መከታ ነው ፡፡...» ብሏል ፡፡

———O———



ተምቤን አውራጃ በአይሮፕላን ተደበደበ ።



በተምቤን የሚበሩ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ።




እግረኛው የኢጣሊያ ጦር ወደተንቤን ተንቀሳቀሰ ።




እግረኛው ተጓዘ ።




ጥይት የተጫኑ ግመሎች ።




ፈረሰኛው ክፍል በሰልፍ ወደተንቤን ሲጓዝ ።




በተንቤን አውራጃ



የተንቤኑ ወጊያ




ኢጣሊያኖች የተምቤን መንደሮች አጋዩ።




ኢጣሊያኖች በተምቤን ምሽጋቸው ።



የተምቤኑ ጦርነት ።



በተምቤን አልቀው በተምቤን የተቀበሩ የኢጣሊያኖች መቃብር




በተምቤን ያለቁ ኢጣሊያኖች የመቃብር ሥፍራ መግቢያ በር